# የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ) እኛነታችንን እንከላከል

እኔነት ስር በሰደደበት ዘመን ተፈጥረናልና እኝነታችንን ለመከላከል ታሪክ ያስገድደናል።ጨለማ በተባለበት ዘመን ተፈጥረሮ በወቅቱ ሃያላን መንግሥታት ሐገሬን አላስነካም ብሎ ክቡር ሂወቱን በገዛ ጥይቱ ለኢትዮጵያ ፍቅር ጥማት ጠጥቶ የተሰዋው የአጼ ቴወድሮስ ታሪክ መነሻችን ነው። የአጼ ሚኒሊክ፣ የበላይ ዘለቀ፣ የባልቻ አባናፍሶ፣የሸዋረገድ፣ የጣይቱ የዘራይ ደረስ፣ የአብዲሳጋ ወዘተ። የአጥንትና የስጋ ምርግ የሆነች ኢትዮጵያን ታሪክን ታሪክ ዓድርገው አንድነቶን በከርስና በስልጣን ሳይሸጡ አቆይተውልናልና የኩራታችን ምንጭ ናቸው።
ሳንፈጠር ተፈጥረው የነበሩት ታላላቆቻችን ለዲሞክራሲ ምስረታ አይከፍሉ መሰዋትነት የከፈሉ የትላንት ወጣቶች፣ ለጽናታችው መሰረት የሆነው ተስማምተው ያወጡትን የውስጣቸውን ደንብ በደም በመጠበቃችው እንደሆነ ታሪካቸው ያስተምረናል።

ሕጋቸውን በሕገወጥነት ሲያረክሱት በብዙሃኑ አልገዛም ሲሉ ተከታዩ ክፍፍልና ፍርሻ እንደሆነና ገመናን ለጠላት ማስጣት እንደሆነ ድርሳናቸውን አገላብጠን የተከሰተውን ችግር በጥሞና መርምረን ተረድተናል ።
ድልን ሳይሆን ትግልን እንደውርስ ተረክበናል። እኛ ወጣቶች የሀገርን እና የወገንን የኢትዮጵያን ጣእም ፍለጋ እነሆ እንደጨው ተበትነን ሀገር አልባ እንዳንሆን በሀገር ውስጥም በውጭም ተደራጅተን ትግል ከጀመርን አመታትን እያስቆጠርን ነው።

በኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ከተደራጀን ገና ሶስት ዓመት እንኮ ባይሞላንም የእትዮጵያን ጠላቶችና ከጠላት ያደሩ ምልምል ጠላቶችን ስላወቅን ተጠይፈናቸዋል። ይዋል ይደር እንጂ አህያ የጅብ ነች እንዳሉት የኢትዮጵያን ጠላቶች ከተጣበቁበት ህልውና ላይ እንደሙጃሌ ነቅሰን እደምናወጣቸው ምንም ጥርጥር የለንም። ሀገራችንን በቁም ለባእድ እየቸረቸረ መቆሚያና መገለጫ ሊያሳጡን የሚቅበዘበዘው የደደቢት ተምቾች የወያኔ ቡድን ዛሬ ደገሞ በውጭ የምንገኘውን ኢትዮጵያኖችን ለማምበርከክና ለማሰገድ ተቆሞቻችን ላይ የተደራጀ የማፍረስ ዘመቻ መያዙን በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የኢሕአፓ ወጣቶች በውል ተረድተናል።

በወያኔ ስር አንበረከክም ያሉ ቤተ ሃይማኖቶችንም ለመቀማት አሰፍስፏል በዚህም ሳያቆም የኢትዮጵያዊ እድሮችን፣ ስብስቦችን፣ ባገኘው ቀዳዳና በተገዙለት ከርሳሞች አማካኝነት በመበታተንና በስሩ ለማስነጠፍ የብር አይነት እየዘራ ይገኛል።

ከሰሞኑ በስደት የሚገኙ አባት እናቶቻችን ታላላቅ እህት ወንድሞቻችን ሳንፈጠር ጀምረው ዛሬ 29 ዓመት ያደረሱትን መሰባሰቢያ የስፖርት ፌደሬሽናችንን በውስጡ ሆነው ሲቦረቡሩ የነበሩ ብኩርነታቸውን በጭብጥ ምስር የለወጡ አሳፋሪ ግለሰቦች ለኝ ለወጣቶች ምን እያስተማሩን ነው? ክሕደትን ተገዢነትን ምርኮኝነትን የመሳሰሉ ገብረጠል ክስተቶችን እያሳዩን ነው። ወገንን ሐገርን በገንዘብ እንደ ይሁዳ መሸጥ ሕጋዊና ባህልአዊ ለማድረግ የሚደረገውን መቅበጥበት እኛ ወጣቶች በጽኑ እንኮንነዋለን።

የኛነት ጉዳይ ነውና በቀላሉ የምንይዘው አይደለም ። አያያዙን አይተው ጭብጦውን ቀሙት ይሆናል። አምስትሺና አስርሺ ምእመናን አዋጥቶ የገዛውን አቢያተ ክርስቲያኖች ቁልፈና ማህተም የያዘ አንደ አለሌ እየቀሙ የስደተኞቹ ላብና ደም የፈሰሰበትን ቤተአምልኮ እንዲሁም ስደተኛው በስደቱ ያስከበረውን ኢትዮጵያዊነት ለወያኔ አሳልፈው የሰጡ ሃሳዊዎችን ገና ሳንከላከል አነሆ ዳግም 29 ዓመት በሰሜን አሜሪካ ያለውን ወጣቶች የወገንና የሐገር ፍቅር እንዲያድርብን እያደረገ ያለውን የግርኮስና የስፖርት ፌዴረሽን በጥቅሉ የመሰባሰቢያ የአንድነት አንባችን የሆነውን የደፈሩትን ሁለትና ሶስት የአላሙዲ እና የወያኔ ተነጣፊ የሆኑ ግለሰቦችን ለመታገል እኛ እኛናታችንን ለማስከበር በሚደረገው ትግል በዓለም ዙሪያ የምትገኙ ወጣቶች ሁሉ ተሳታፊ እንድትሆኑ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን።

በምንደኞች ኢትዮጵያና ህሴቶቿ አይጠፉም
የኢትቶጵያን ተቃሞቻችን እንከባከብ
የሰሜን አሜሪካ የስፖርት ፌዴሬሽን 29ኛው ዓመት በዳላስ ከወያኔ በጸዳ መንፈስ ይከበር

**ኢወክንድ እናቸንፋለን!**

Joineprpyl@gmail.com office- 202 291 5832 http://eprpyl.com/
www.facebook.com/eprpyl